# አማኑኤል ሆይ

አማኑኤል ሆይ መድኃኒቴ ሆይ
አትተወኝ አንተ ሞትን እንዳላይ (2)

የግብጽ ከተማ ደምቃ ስትታይም
ተሰሎንቄ አድጋ ለአይኔ ስትስበኝ
ኤልሻዳይ ኢየሱስ ልቤን መልስልኝ (2)

አዝ

መታመን በሰው ላይ ለእኔ አይሆንም
መከታነት በሰው ከቶ አይጠቅምም
አትተውኝ አንተ አምላክ ዘላለም
አትተወኝ አንተ መድኃኔዓለም

አዝ

የሚያጽናናኝ የለም እኔ እንዲህ ስከፋ
ህልምም ሆኖብኛል የሰው ሁሉ ተስፋ
ቃልን የማታጥፈው አንተ ከእኔ አትጥፋ (2)

# እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው (2)

ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሶብን ሳለ በእኛ በሁላችን
ቃል እንደተገባለት ተወልዶ ሊያድነው
በመከራ ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው/2/

አዝ

አብርሃም ከካራ ከእናት ከአባቱ ቤት
ከነአን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎልበት
እንደ ምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት/2/

አዝ

በሐዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ቢነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ሐዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ቢነሳኝ
ክርስቶስ እየሱስ ሐዘኔን አስረሳኝ